<u>ሰኔ 2 ቀን 2003 ዓ.ም</u>

<u>ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ</u>

<u>የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ</u>

<u>የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርት</u>

<u>አጭር መግለጫ</u>

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101/2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 18 እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ (Protection of Basic Services) ፕሮግራም የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማዎች ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፤ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ያስገኙት ውጤት ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ እና ተፈላጊውን ግብ የመታ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ፣ በዚሁ መሠረት በ2002 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የተከናወኑ ኦዲቶች ሪፖርትና የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ዕቅድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፣

1. በልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔና አካባቢ ኦዲት እና ልዩ ኦዲቶች፣ እንዲሁም በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮግራም ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ (Protection of Basic Services) ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶችን የያዘ ነው::

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች የተመረመሩትን በውጭ እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያካትታል::

3. በዚህ ሪፖርት ውስጥ የሚቀርቡ የ2002 በጀት ዓመት የተለያዩ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድና ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም የተከናወኑ ተግባራት፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ ይዞታ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው::

4. የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች ለም/ቤቱ የቀረቡ ሲሆን እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንዲደርስ ተደርጓል::

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተፈጸመ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit conference) ከመደረጉም ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል::

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት

በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው::

የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ

7. የ2002 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ዕቅዳችን መሠረት ያደረገው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትንና አዲሱን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 63/2 መሠረት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳባቸውን በመዝጋት ለኦዲት ማቅረብ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በሌላም በኩል መ/ቤታችንም በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች ሂሳባቸውን ዘግተው ሲያቀርቡ ኦዲቱን በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ታህሣሥ 30 በማጠናቀቅ ሪፖርቱን ለኦዲት ተደራጊዎች ለመስጠት ግብ ጥሏል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችለው የኦዲት ካላንደርና ዘዴ ላይ ለውጥ በማድረግ ኦዲቱ የሂሳብ መዝጋትን ሳይጠብቅ በየዓመቱ በጥር ወር ተጀምሮ በተከታዩ ዓመት ታህሣሥ ላይ የሚጠናቀቅበት ሥርዓት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

8. በዚህም መሠረት በ2002 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 164 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ የተደረጉትን 14 መ/ቤቶች ጨምሮ በ144 መ/ቤቶች የኦዲት ሥራ በማከናወን የኦዲት ሽፋኑን 87.8% ለማድረስ መታቀዱ ይታወሳል፡፡ በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ ከታቀዱት 130 መ/ቤቶች መካከል አንዱ ሲታጠፍ የቀሩት የ129 መ/ቤቶች እና በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን በኩል ኦዲት ለማድረግ የታሰቡት 14 በድምሩ የ143 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት በመከናወኑ የኦዲት ሽፋኑን 87.19% ለማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ አካላት በቀረቡ ጥያቄዎች መሠረት 5 ልዩ ኦዲቶች ተከናውነው ሪፖርቱ ለሚመለከተው ተልኳል፡፡

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

9. የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን 129 በሚሆኑ የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ276 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም (ልዩ ኦዲትን ሳይጨምር) ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2001 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ.	መግለጫ	በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት	
		2001	2002
1	አጥጋቢ ሆነው በመኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Clean opinion)	5	49
2	አልፎ አልፎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion)	51	50
3	አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ አስተያየት የተሰጠባቸው (Disclaimer of Opinion)	5	8
4	የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው (Adverse Opinion)	10	14
5	ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው	N/a	8
	ድምር	71	129

<u>በፌዴራል መንግሥት የልዩ ልዩ መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች</u>

10. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕጉን፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በ2002 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሣብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች ያጋጠሙ ሲሆን የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ ይገባል ተብሎ የታመነባቸው አንኳር አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

<u>ውዝፍ የሰነድ/ተሰባሳቢ/ ሂሣብ</u>

11. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ43 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 887.49 ሚሊዮን ውዝፍ የሰነድ/ተሰብሳቢ/ ሂሣብ ተገኝቷል:: ከዚህ ውዝፍ የሠነድ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 340.92 ሚሊዮን፤ በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጠና ብር 121.70 ሚሊዮን፤ የመከላከያ ሚኒስትር ብር 117.06 ሚሊዮን፤ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 114.31 ሚሊዮን፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 78.63 ሚሊዮን፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 25 ሚሊዮን፤ በግብርና ሚኒስቴር የምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት ብር 12.32 ሚሊዮን እና ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ብር 12.16 ሚሊዮን ይገኙበታል::

12. ውዝፍ የሰነድ ሂሣቡ በየመ/ቤቶቹ የሥራ ማስኬጃ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የሥራ እንቅስቃሴ የሚያዳክምና የበጀት አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለምዝበራና ለብክነት በር የሚከፍት በመሆኑ መ/ቤቶቹ የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው እንዲያወራርዱ አሳስበናል::

<u>የገቢ ሂሣብ</u>

13. የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል::

በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ

14. በ10 መ/ቤቶች ውስጥ ብር 4.38 ሚሊዮን በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሰበሰብ ተገኝቷል:: ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች ሊሰበሰብ ይገባ የነበረው ብር 3.67 ሚሊዮን ሲሆን ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (Harmonized System Code) እና (Custom Procedure Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሠረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሠረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

15. በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

በወቅቱ ገቢ ያልተደረገ ውዝፍ ሂሣብ

16. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ ስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 285.38 ሚሊዮን በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ ተገኝቷል::

17. ገቢን በወቅቱ መሰብሰብ መንግሥት ለሚያከናውነው የልማት ሥራዎች ወሳኝ በመሆኑ ለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ አሳስበናል::

በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ
የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

18. የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሥር ባሉ ሦስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች ሶስት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 58.64 ሚሊዮን የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት ገቢው ከማን እንደተሰበሰበ ሳይገለጽ በኮድ በመሰብሰቡ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤

- 9 መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢ የሰበሰቡት ብር 543.29 ሚሊዮን መ/ቤቶቹ ባቀረቡት ዓመታዊ የየመ/ቤቶቹ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት መገኘቱ፤

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ሳይታወቅ ጥቅል ዋጋውን (CIF Value) በመውሰድ በአንድ የታሪፍ ቁጥር ላይ በመመደብ በ20% የጉምሩክ ቀረጥ ምጣኔ ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን፤ ከነዚህ ዕቃዎች ውስጥ በ30% እና በ35% የቀረጥ ምጣኔ መሠረት ሊስተናገዱ የሚገባቸው እቃዎችም መገኘታቸው፤

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የማስጫኛ እና ኢንሹራንስ ደረሰኝ በአስመጪዎች በማይቀርብበት ጊዜ ለማስጫኛ ዋጋ የFOB ዋጋውን 10%፣ ለኢንሹራንስ ደግሞ የFOB ዋጋና የማስጫኛውን ድምር 5% በመውሰድ ቀረጥና ታክሱ የሚሰላ ሲሆን አሰራሩም ለረጅም ጊዜ የቆየ ከመሆኑም በላይ በመመሪያ ያልተደገፈ እና በልምድ ሲሰራበት የቆየ መሆኑ፤

- ለኦዲት ከተመረጡ ዲክላራሲዮኖች ውስጥ ከባንክ የተፈቀደላቸው የውጪ ምንዛሪ ቀረጥና ታክስ ከተከፈለበት የእቃ የዋጋ ጋር ሲነጻጸር፤ በድሬዳዋ እና በአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ዋጋ በባንክ ከተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ በUSD 4,334,624.02 ብልጫ ሚያሳይ በመሆኑ

አሠራሩ ህጋዊ ያልሆነ የውጭ ምንዛሪ ግብይትንና በአገሪቱ የፋይናንስ ተቋማት በኩል የማይታወቅ የገንዘብ ዝውውር እንዲኖር የሚያደርግ መሆኑ፤

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ ግልጽ የሆነ ጥፋት በፈጸሙ አንዳንድ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ላይ በአፈፃፀም መመሪያው መሠረት አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ በድሬዳዋና በአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ለገባ ዕቃ እና በሰነድ አለመሟላት ምክንያት በዋስትና የተያዘ ሂሣብ፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዋስትና የተያዘ ሂሳብ፣ የቦንድ ጊዜ ያለፈበትና የዕቃው ቆይታ ጊዜ ፈቃድ በባለስልጣኑ ያልተራዘመላቸው በድምሩ ብር 302.97 ሚሊዮን የዋስትና ጊዜ ገደቡ ቢያልፍም በመመሪያው መሠረት ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተላለፈ መሆኑ፣

- የቫውቸር ተጠቃሚዎች ወደ አገር ውስጥ ያስገቡት የጥሬ እቃም ሆነ ወደ ውጭ የተላከውን ምርት መከታተያ ስርዓት ቢኖርም ያልተተገበረ በመሆኑ በመመሪያው መሠረት ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ ካለመቻሉም በላይ ከጠቅላላው የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚዎች ውስጥ 27 ድርጅቶች የተፈቀደላቸው የቫውቸር መጠን በድምሩ ብር 68.77 ሚሊዮን ቀረጥና ታክስ አለማወራረዳቸውና ቫውቸራቸውንም ያላሳደሱ መሆኑ፣

- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤትና የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ መዝገብ ተከፍቶ በየድርጅቶቹ ስም ተመዝግቦ ያልተያዘ በመሆኑ የቅ/ጽ/ቤቶቹ የተሰብሳቢ ሂሣብ አያያዝ ሥርዓት እና የተዘረጋው የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት አስተማማኝ መረጃን ሊሰጥ የማይችል መሆኑ፣

- በባህር ዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ዘግይቶ በተሰበሰበ የደመወዝ ገቢ ግብር እና የቅድመ ታክስ በድምሩ ብር 3,033,014.15 በወቅቱ ገቢ ባላደረጉ ግብር ከፋዮች ላይ ቅጣትም ሆነ ወለድ ያልተጣለባቸው መሆኑ፣

- በምሥራቅ አዲስ አባባ ቅ/ጽ/ቤት 12 ግብር ከፋዮች የኤክሣይዝ ታክስ፣ በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት 4 ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጁ መሠረት ሪፖርት ያላደረጉ መሆናቸው፣

- የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በፍሪላንስ ዜና አንባቢነትና ዘጋቢነት በኮንትራት ቅጥር ከሚያሰራቸው ሠራተኞች የሚቀንሰው የሥራ ግብር በኮንትራት ውሉ መሠረት ድርጅቱ በሚከፍላቸው ደመወዝ ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ በአዋጁ መሠረት ሊሰበሰብ የሚገባው የሥራ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

- የጎንደር የሕክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን የውስጥ ገቢ፣ የልዩ ፋርማሲ የመድኃኒት ሽያጭ ገቢና የፕሮጀክት ፈንድ ለይቶ አለመመዝገቡ፤

- የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርን ሣያሣውቅና ፈቃድ ሣያገኝ ብዛቱ 5000 የሚሆን ጥራዝ የውስጥ ገቢ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ አሣትሞ እየተጠቀመበት መገኘቱ፤

19. ስለሆነም መ/ቤቶች ያልተሰበሰበው የመንግሥት ገቢ እንዲሰበሰቡ ለወደፊቱ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ፤ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት ከመንግሥት ገቢ አሰባሰብ ጋር የተያያዙ የአፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የወጪ ሂሣብ</u>

20. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሳቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ

በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

21. በ16 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 1.45 ቢሊዮን በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 1.42 ቢሊዮን ዝርዝር ሥራ በሚያሳይ ማስረጃ ሳይደገፍ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ ብቻ ለጂ.ቲ.ዜ የተከፈለ፣ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 17.10 ሚሊዮን የግንባታ ክፍያ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት የዓለም አቀፍ አባልነት መዋጮ ብር 2.74 ሚሊዮን በባንክ የተላከ እና የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 6.97 ሚሊዮን እና ሌሎችም ከእቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይኖር እንዲሁም የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ እንደወጪ ማስረጃ በመያዝ በወጪ የተመዘገቡ ይገኙበታል፡፡

22. ማንኛውም ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያ መሠረት ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች

23. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ32 መ/ቤቶች ብር 83.34 ሚሊዮን የመንግሥትን የግዢ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ግዥ ከፈጸሙት መ/ቤቶች መካከል ትምህርት ሚኒስቴር ብር 27.80 ሚሊዮን (ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ ማስፋፊያ ግንባታና የኮምፒዩተር ግዥ)፤ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 11.94 ሚሊዮን (ለሠራተኞችና መምህራን መኖሪያ ሕንፃ ግንባታ)፤ የወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 8.92 ሚሊዮን (ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት)፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 5.51 ሚሊዮን እና የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ድርጅት ብር 5.6 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

24. የግዢ መመሪያን ሳይከተሉ የዕቃ ግዢ መፈጸም ለምዝበራ፣ ለጥፋትና ጉድለት የሚዳርግ በመሆኑ የመንግሥት የዕቃ ግዢ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

25. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ22 መ/ቤቶች ብር 584.61 ሚሊዮን ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ የትምህርት ሚኒስቴር 13 ዩኒቨርስቲዎችን ለማስገንባት በተገባው ውልና በተፈፀመው ክፍያ መካከል ብር 441.2 ሚሊዮን ከውሉ በላይ ክፍያ የተፈጸመ፤ የውሃና ኢናርጂ ሚኒስቴር በውሃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ለሠራው ሥራ መጠን በምስክር ወረቀት ሳይረጋገጥ 112.5 ሚሊዮን፤ እንዲሁም ከክፍያ መቀነስ የነበረበት ብር 20.2 ሚሊዮን በድምሩ ብር 132.7 ሚሊዮን ከደንቡ ውጪ የተከፈለ እና ሌሎችም ከገቡት ውል ውጭ ክፍያ በመፈጸም፤ ሂሳቡን ሁለት ጊዜ በወጪ በመያዝ፤ በሂሳብ ስሌትና በስምምነቱ ከተቀመጠው ዋጋ በማስበለጥ የተከፈለ ይገኝበታል፡፡

26. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ

27. በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች በሕጉ መሠረት የተፈቀዱ፣ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ብር 2.36 ሚሊዮን በወሎ ዩኒቨርሲቲ፣ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

28. በመሆኑም ለሂሣቦቹ ደጋፊ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፣ ይህ ካልሆነ ገንዘቡ ለመንግሥት ሳጥን እንዲተካና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ ለመ/ቤቶች አሳስበናል፡

የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት

29. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃ ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ8 መ/ቤቶች በብር 10.95 ሚሊዮን የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ በኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ

ማዕከል በብር 8.9 ሚሊዮንና የጅማ ዩኒቨርሲቲ በብር 1.34 ሚሊዮን የተገዛውን ቋሚ ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ዋንኞቹ ናቸው፡፡

30. የተገዙት ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ሂሣቡን በወጪ መመዝገብ ለመንግሥት ንብረት መባከን መንስዔ በመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትና የተጠቀሰው ሂሣብ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ እሳስበናል፡፡

አላግባብ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ

31. በበጀት ዓመቱ በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ7 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 265.25 ሚሊዮን በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 115.69 ሚሊዮን፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 112.06 ሚሊዮን እና ጂማ ዩኒቨርሲቲ 37.5 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

32. በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው ወይም በሚፈቅደው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብለት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ ለየመ/ቤቶቹ አሳስበናል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

33. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ20 መ/ቤቶች ብር 247.20 ሚሊዮን በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፤ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 117.31 ሚሊዮን፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 56.99 ሚሊዮን፤ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 28.15 እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 26.99 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

34. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ በተመለከተ የፋይናንስ ሕጉንና የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ መመሪያን ተከትለው እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

የበጀት አጠቃቀም

35. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት በ22 መ/ቤቶች ብር 764 ሚሊዮን በዋና ዋና የወጪ ሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ዝውውር ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ አድርገው ተገኝተዋል። ዋና ዋናዎቹም ትምህርት ሚኒስቴር ብር 693.6 ሚሊዮን፤ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 21.7 ሚሊዮን፤ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 17.9 ሚሊዮንና ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር15.2 ሚሊዮን ይገኙበታል፡፡ በሌላም በኩል በ33 መ/ቤቶች ለዋና ዋና የወጪ ሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ውስጥ ብር 652.3 ሚሊዮን ስራ ላይ ሳያውሉት ተገኝተዋል።

36. በመሆኑም መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸውና፣ የበጀት ጥያቄያቸው በበቂ ጥናት የተደገፈ፣ እንዲሁም ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበት አሳስበናል።

የንብረት አስተዳደር

37. መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም። በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ፡-

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	12 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	3 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	22 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	16 መ/ቤቶች
የቋሚ ዕቃ ቆጠራ ተደርጎ ከመዝገብ ጋር ሲመሳከር በታየው	1 መ/ቤት

ልዩነት ላይ እርምጃ ያልወሰደ	
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	14 መ/ቤቶች

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

38. በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያከናውኑ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ተሽከርካሪ

39. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል።

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ8 መ/ቤቶች	271 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ13 መ/ቤቶች	186 ተሽከርካሪዎች
የሻንሲና ሞተር ቁጥር ከሊብሬ ጋር ተቀያይሮ ተመዝግቦ የተገኘ	በ1 መ/ቤት	2 ተሽከርካሪዎች
የቻሲና የሞተር ቁጥራቸው የማይታወቅ	በ2 መ/ቤቶች	10 ተሽከርካሪዎች
ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ	በ1 መ/ቤት	3 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል።

40. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ፣ የቻሲና የሞተር ቁጥራቸው የማይታወቅ እና ሊብሬ ያልቀረበላቸው ደግሞ ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል።

መሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS)

ተከታታይ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች

41. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት በየሩብ

ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍናቸው ሴክተሮች በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የውሃና የገጠር መንገድ ሴክተሮችን ነው፡፡

42. የ PBS II ስምምነትን ተከትሎ በተሻሻለው የኦዲት ስምምነት መሠረት ተከታታይ ኦዲቱ በሀጋዊነት (Fiduciary Responsibility) ላይ እንዲያተኩር ተደርጎ፤ የኦዲት ውጤቱ የፕሮጀክቱ ሂሣብ ዓመታዊ ኦዲት አካል እንዲሆን በተወሰነው መሰረት ተከናውኗል፡፡

43. በዚህም መሠረት በሁሉም ክልሎች በ250 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ የክልል ሴክተር ቢሮዎች ተከታታይ ኦዲት (Continuous Audit) እና አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነ የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ በ276 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም ፕሮግራም አቀፍ የሆነውን የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደረጃ በማካሄድ የPBS ኦዲቱን በታቀደው መሠረት ለመፈጸም ተችሏል፡፡

44. በ2002 ለ PBS II የተመደበ በጀት ሂሣብ ላይ በተከናወኑ የተከታታይ ኦዲቶች (continuous Audit) በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የክልል መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው ሲሆን፣ ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- ለቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ መቆጣጠሪያ የሚረዱ ደጋፊ ሌጀሮች (Subsidiary ledgers) አለመቋቋማቸውና፣ በወቅቱ አለመወራረዳቸው፣
- የሂሣብ እንቅስቃሴዎች (Transactions) በወቅቱ አለመመዝገባቸው፣
- ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫዎች በአብዛኛው በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ክፍል አለመላካቸው፣

- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው መ/ቤት አለመቋቋም፣
- ቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ፣ እና
- በኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ አስተያየቶች ላይ እርምጃ አለመወሰድ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

45. ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሚሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡-

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የበጀት እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና መኖርና፣ የግንዛቤ ማነስ፣ እንዲሁም
- የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለጉዳዩ በቂ ትኩረት አለመስጠት፤

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

<u>በልዩ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲቶች ውጤት</u>

46. መ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከልዩ ልዩ የመንግሥት አካላት የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች እየገመገመና ካለው የሰው ኃይል አንፃር እያገናዘበ ልዩ ኦዲት የሚያከናውን መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሠረት ከጥር 2002 እስከ ታህሣሥ 2003 5 ልዩ ኦዲቶች በጥያቄ ተሠርተው ሪፖርቱም ለጠያቂው አካል ተልኳል፡፡

እነርሱም :-

- በፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥያቄ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ፕሮጀክት የሲሚንቶና ብረታ ብረት ግዥ እና በአገር አቀፍ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም ለድሬዳዋ ገጠር ከተሞች የኤሌክትሪክ ማስፋፊያ የተገዙ ትራንስፎርመሮችና አሉሚኒየሞች በተመለከተ የተከናወነ ልዩ ኦዲት፤
- በሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ጥያቄ የቀድሞው የአዲስ አበባ የማገዶ እንጨት ተሸካሚ ሴቶች ማሕበር ሂሳብ ላይ የተከናወነ ልዩ ኦዲት፤

- በትግራይ ብ/ክ/መ/ምክር ቤት ጥያቄ የክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሂሣብ ላይ የተካሄደ ኦዲት፤
- በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ጥያቄ በከተማው አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሂሳብ ላይ የተካሄደ ኦዲት፣

ናቸው፡፡

የፌዴራል የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት በተመለከተ

47. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ተከናውኖ የተጠናቀቀ ቢሆንም የመውጫ ስብሰባ ባለመደረጉ ውጤቱን በዚህ ሪፖርት ውስጥ ማካተት አልተቻለም፡፡

የክዋኔና አካባቢ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች በተመለከተ

48. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትን ተከትሎ መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱን ሽፋንና ጥራት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በሂደት ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ የማድረግ አቅጣጫን ለመከተል መወሰኑም ይታወቃል፡፡ በዚህም መሠረት በ2002 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውንና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መወጣታቸውን ለማረጋገጥ ቀደም ሲል የተጀመሩ ኦዲቶችን ጨምሮ በ17 መ/ቤቶች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ላይ የክዋኔ ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ 14 የሚሆኑ የክዋኔ ኦዲቶችን ወይም የዕቅዱን 82.35% በማከናወን ሪፖርቱ በ14 ጥራዞች ተዘጋጅቶ ለም/ቤቱ ቀርቧል፡፡ ኦዲታቸው ከተጠናቀቀው 14 በተጨማሪ 5 የሚሆኑ የክዋኔ ኦዲቶች ሥራቸው ተጀምሮ ሳይጠናቀቁ ወደያዝነው የኦዲት ዓመት የተሻገረ ሲሆን የተጠናቀቁት ክዋኔ ኦዲቶች ዋና ዋና ግኝቶች ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

49. በውኃ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የከሰም ተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት (Irrigation) ላይ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

- በከሰምና ተንዳሆ መስኖ ልማት ላይ የተመረኮዘ ወቅታዊ ሁኔታዎችን የሚያሳይና በጥናት ላይ የተመሰረተ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ያልተዘጋጀለት መሆኑ፣
- ስለማህበራዊ ጉዳዮችም በቅድሚያ ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ውይይትና የግንዛቤ ማዳበር ስራ አለመሰራቱ፤
- የፕሮጀክት አስተባባሪ ጽ/ቤቱ የመስኖ ልማት ግንባታውን የሚቆጣጠርበት፣ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ የመስኖ ልማቱ መሬቶች ርክክብ እስኪደረግባቸው ድረስ የሚደረገው የጥበቃ ስርዓት ያልተጠናከረና የተሰራውን ስራ ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑ፤
- ለፕሮጀክቱ ስራ መጓተት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት ችግሮች መካከል አንዱ ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር የተፈጠረው አለመግባባት ሲሆን፣ ይህንንም ችግር በዋነኝነት ከሚያባብሱት ምክንያቶች አንዱ ማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከልና ለአካባቢው ነዋሪዎች እንዲውል የታቀደው የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ቅድሚያ ተሰጥቶት ባለመገንባቱ መሆኑ፤

50. በትምህርት ሚኒስቴር የዩኒቨርስቲ አቅም ግንባታ ፕሮግራም የአሥራ ሦስት ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ላይ የተካሄደ ክዋኔ ኦዲት

- የግንባታው ዲዛይን በየጊዜው ለውጥ መደረጉ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲወጣ ምክንያት ከመሆኑም በላይ በተማሪዎቹ ላይ ችግር መፍጠሩ፤
- በናሙና ከታዩት ስድስት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ሶስቱ፤ የሚዛን ቴፒ፣ የመደውላቡና የዲላ ዩኒቨርስቲዎች የሳይንስ ፋክልቲዎች የላብራቶሪ መሳሪያ

ስለሌላቸው ተማሪዎች ወደተለያዩ ክልሎች በመሄድ ለነባር ዩኒቨርስቲዎች ክፍያ በመክፈል ትምህርት እንዲያገኙ መደረጉ ተጨማሪ ወጪን ማስከተሉ፤

- ትምህርት ሚኒስቴር ለዩኒቨርስቲዎቹ ማሰሪያ የሚከፍለውን ወጪ፤ የወጪውን አይነት የገንዘቡን ልክ፣ የግንባታውን ደረጃ እንዲሁም ጊዜውን የሚያሳይ መቆጣጠሪያ መረጃዎች አለመያዙ ፕሮጀክቶቹን በሚገባ ለመቆጣጠር ያላስቻለው መሆኑ፤

- በአብዛኛዎቹ ዩኒቨርሲቲዎች ከጊዜያዊ ርክክብ በኂላ በአያያዝ ጉድለት የሚከሰቱ ጥፋቶችን ተከታትሎ ለመጠገን የሚችሉ የጥገና ስራ ክፍሎች ባለመኖራቸው ችግሮቹ ሊባባሱ ችለዋል፡፡

- የግዥውና የግንባታው እቅድ አፈፃፀም ያልተጣጣመ መሆን ተገዝተው የሚመጡ ዕቃዎች አመቺ ባልሆነ ቦታ ተቀምጠው ለብልሽት እንዲጋለጡ ሊያደርግ ችሏል፡፡

51. <u>በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በቡና ምርምር ኘሮጀክት ላይ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

- ከአገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር ተገናዝበው የሚካደፉ የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሥራ ሂደት ወጥነት እንዲኖረው የሚያስችል፣ በአግባቡም ተዘጋጅተው የሚካደፉ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ያስገኙትን ውጤት ለመገምገምና ተፈጻሚነታቸውንም ለመከታተል የሚያስችል የስራ መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

- የምርምር ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስራው መጀመር እና መጠናቀቅ ሲገባው ስራው በተያዘለት የሥራ ዘመን ሊጠናቀቅ አለመቻሉና ተጨማሪ አዳዲስ ተግባራት ታክለውበት የስራ ዘመኑ ለተጨማሪ 5 ዓመታት (ከ1998-2002) የተራዘመ ቢሆንም፤ ፕሮጀክቱ ቀደም ብሎ በተያዘለት የሥራ ዘመን መሰረት ያልተጠናቀቀበትን ምክንያት በስራ ዘመኑ ማብቂያም ከዕቅዱ ምን ያህል እንደተጠናቀቀ እና እንዳልተጠናቀቀ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና በጎ የስራ ተሞክሮዎች ተለይተው ሪፖርት አለመደረጋቸውና ዝርዝር ሁኔታውን ለመገንዘብ አለመቻሉ፤

- በፌዴራልና በክልል የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አላስፈላጊ የሆነ የስራ ድግግሞሽና የሐብት መባከን እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክት ግምገማ ስርዓት አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር መዘርጋት ለኢንስቲትዩቱ የተሰጠ የስራ ኃላፊነት ቢሆንም ወጥነት ያለው ስራ ለመስራት የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

- በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተሰጠውን የስራ ኃላፊነት ውጤታማና ስኬታማ ሊያደርግ የሚያስችል የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ስርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

52. <u>**በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአትሌቲክስ ስፖርትን በአገሪቱ በማስፋፋት ብቃት ያላቸውን አትሌቶች ለማፍራት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በተመለከተ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት**</u>

- አትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ብሎም ሀገሪቱን ወክለው በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ በሚዘጋጁ የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ የሚወዳደሩ ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት በሁሉም ክልሎች ከታች ከቀበሌ እና ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ ተገቢው ትኩረት ተሠጥቶት ስፖርቱን ለማስፋፋት የሚያስችል አደረጃጀት ባለመዋቀሩ፤ በአትሌቲክስ ስፖርቱ ዙሪያ ለሚከሠቱ ችግሮች ተገቢውን ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ድክመት መታየቱ፤

- ለታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች ሥልጠና፣ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ የባለድርሻ አካላት አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ያልተቀመጠ ሲሆን፣ ስፖርቱ በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲዘወተር እና እንዲስፋፋ ለማድረግ የተቀናጀ እና ወጥ አሠራርን የተከተለ የአተገባበር ስልት አለመቀየሱ፤

- በመሆኑም ፌዴሬሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ወቅታዊ መረጃዎችን በተገቢው መንገድ በመለዋወጥና፤ በመተባበር የተጠቀሱትን ችግሮች በማስወገድ አገርቷ በዘርፉ ሊታገኝ የሚገባትን ውጤት ለማሳካት ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

53. **<u>የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለከተ የተካሄደ ክዋኔ ኦዲት</u>**

- የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ዙሪያ በአዋጁ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈፀም፣ ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ራሱን የቻለ አደረጃጀት ያልዘረጋ መሆኑ፤

- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለወጪ መጋራት ሥራ በባለሙያ ደረጃ ባስቀመጠው መደብ ላይ የሰው ኃይል ያልመደበ በመሆኑ፣ የወጪ መጋራትን የተመለከቱ ሥራዎችን በተደራቢነት ክፍያ ሊፈጽሙ የሚመጡ ተጠቃሚዎችን ብቻ በማስተናገድ መወሰኑ፤

- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት የመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) የሌለው ሲሆን የወጪ መጋራት ክፍያ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶም በቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና ውክልና በሰጣቸው ከተማ/ክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ መጋራት ክፍያ መሰብሰቡን እና ፈሠስ መደረጉን በየ6 ወሩ መከታተል ሲገባው ፈሰስ የሚያደርጉለትን እና የማያደርጉለትን ክልሎችም ለይቶ አልያዘም፡፡ ይህም በመሆኑ በናሙና ከታዩ 3 የክልል/ከተማ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና 2 ድርጅቶች ብቻ ከወጪ መጋራት የተሰበሰበውን ብር 10,859,248.66 ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ፈሰስ ሳይደረጉ እንደየራሣቸው ክልል ገቢ በመቁጠር ተጠቅመውበት ወይም ፈሰስ የሚያደርግበትን የባንክ ሂሣብ ቁጥር ባለማወቃቸው ገንዘቡ ሥራ ላይ ሳይውል እና ፈሠስ ሳይደረግ በአደራ ወይም በተከፋይ ሂሣብ ይዘውት መገኘቱ፤

- ባለሥልጣኑ የወጪ መጋራት ክፍያን የፈፀሙ/እየፈፀሙ ያሉ ተጠቃሚዎችን፣ የአሠሪ ድርጅቶች፣ እንዲሁም የተመራቂ ተማሪዎችን ዝርዝር መረጃ በተሟላ ሁኔታ በዳታ ቤዝ ባለመያዙ በሀገሪቱ ካሉት 22 ተቋማት እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ ያስመረቋቸውን ተጠቃሚዎች ዝርዝር መረጃ በተሟላ ሁኔታ ለባለሥልጣኑ የላኩት 7ቱ ብቻ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

- አሠሪ ድርጅቶች የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ተጠቃሚ ከሆኑ ሠራተኞቻቸው ደመወዝ በየወሩ 10 በመቶ (1/3ኛ) እየቀነሱ ለኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት ገቢ ሊያደርጉ ሲገባ፤ በናሙና ተመርጠው ኦዲት የተደረጉ 3 ሚኒስቴር መ/ቤቶች በጠቅላላ የወጪ መጋራት ተጠቃሚ ከሆኑ ሠራተኞቻቸው በደንቡ መሠረት ከደመወዛቸው 10% (1/3ኛ) ተቀናሽ አድርገው ለባሥልጣን መ/ቤቱ ገቢ የማያደርጉ መሆኑ፤

- በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፤ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተገቢውን አደረጃጀት ፈጥረው በመንቀሳቀስ ለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት መረጃ ልውውጥና ገቢ አሰባሰብ ትኩረት በመስጠት በወጡት ሕጎች፤ ደንብና መመሪያዎች መሰረት ማስፈጸምና ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

54. በግብርና ሚኒስቴር የእጽዋት ፀረ-ተባይ ኬሚካል ምዝገባ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ ሥርዓት ላይ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

- በናሙና ተመርጠው የታዩት 12 የግልና 25 የመንግስት የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ደረጃውን ባልጠበቀ ሁኔታ በመገንባታቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የአገልግሎት እድሜ (Shelf life) እንዲያጥር፣ የፍቱንነት ደረጃቸው እንዲቀንስ እንዲሁም በሰዎች እና በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ ምክንያት ሊሆን መቻሉ፤

- መንግስታዊና የግል ፀረ-ተባይ አስመጪዎች የኬሚካሉን የወል መጠሪያ፣ የድብልቅ መጠን፣ የአጠቃቀም መመሪያ፣ ፀረ-ተባዩ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ አደጋ እንዳያስከትል መቆየት የሚያስፈልግበትን ጊዜ፣ የአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት በወሰነው ምደባ መሠረት አደገኛነቱን የሚያስጠነቅቅ የጽሑፍና ስዕላዊ መግለጫ፣ በአደጋ ጊዜ ሊወሰድ የሚገባውን የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ አሠጣጥ፣ የተመረተበት ቀን እና የአገልግሎት እድሜውን በሚያሳይ መልኩ በፀረ-ተባይ ኬሚካል ማሸጊያዎች ላይ መለጠፍ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም በናሙና በታዩት ድርጀረጅቶች ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- ማንኛውም በፀረ-ተባይ ኬሚካል በማስመጣት ላይ የተሰማራ ነጋዴ ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት መሸጥ ወይም መጠቀም የተከለከለ ቢሆንም፤ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል አስፈላጊው ፍተሻ ተደርጐባቸው ሳይመዘገቡ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና ሥራ ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ ኬሚካሎቹ በሠዎች፣ በእንስሳት፣ በአካባቢ እና በሀገሪቱ የወጭ ግብርና ምርት ንግድ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል መሆኑ፤

- በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና በማስተባበር በመፍታት የጸረ-ተባይ ኬሚካሎች በአካባቢውና በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

55. **<u>የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የግዥና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>**

- ከ 2000 ዓ.ም በኋላ በማእከል እንዲሁም የደቡብ ምስራቅ እና የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤቶች ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተደርጎ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት አለመቅረቡ፤ እንዲሁም በማዕከላዊ ዕቃ ግምጃ ቤት በተደረገው ቆጠራ በድምሩ ብር 2,644,528.80 ብልጫ እንዲሁም ብር 279,328.43 ጉድለት ታይቶ ሪፖርት የቀረበ ቢሆንም፤ የተወሰደ እርምጃ ስለመኖሩ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

- ኮርፖሬሽኑ አቃቂ ከተማ ለነበረው ሬዲዮ መገናኛ ከጥር 14/1963 ዓ.ም. ጀምሮ ከተለያዩ ግለሰቦች ግምት እየተሰጠና በምሪት ያገኘው ስፋቱ 112.5 ሄክታር (1,125,118 ሜ.ካ) መሬት ዙሪያው 4 ኪ.ሜ. በግንብ የታጠረ፤ በአሁኑ ወቅት የቀድሞ ሬዲዮ መገናኛ አሮጌ መሣሪያዎች ያለበት፤ ጥቂት መጋዘኖችና ቤቶች የሚገኙበት የሚወገዱ ዕቃዎች የሚከማቹበት በጣም ሰፊ የሆነው መሬት ያለአገልግሎት ለ40 ዓመታት ያለበቂ አገልግሎት ያለአግባብ የተቀመጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

56. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግሥት ኘሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

- ማንኛውም የልማት ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ በፊት በፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያው መሠረት የአዋጭነት ጥናት እና የዝርዝር ንድፍ (ዲዛይን) ሥራ ሊሠራላቸው የሚገባ ቢሆንም አንዳንድ ፕሮጀክቶች በዚህ መሠረት የአዋጭነት ጥናት ሳይሰራላቸው ወደ ግንባታ ሥራ የገቡ ሆነው መገኘታቸው፤

- አንዳንድ የልማት ፕሮጀክቶች በተዘጋጀላቸው የጥናት ሰነድ ላይ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ እና የገንዘብ መጠን መሰረት እንዳልተጠናቀቁና ተጨማሪ ጊዜ እና ወጪ ማስከተላቸው፤

- በፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት ስለ ፕሮጀክቶች የስራ አፈጻጸም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርበውን የሩብ ዓመት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም የግምገማ እና የተጠቃለለ ሪፖርትና የግምገማ ውጤት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የማይቀርብ መሆኑ፤

- ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋጽኦ አላቸው ተብለው በተለዩት ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ (ex-post evaluation) ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ሥራ ከጀመረ ጥቂት ዓመታት በኋላ ቀደም ብለው በተቀመጡ የፕሮጀክቱ በአካባቢ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉት ተጨማሪ ፋይዳ መሠረት፣ የተገኙ የግብ ስኬቶች እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች እንደማይከናወን;

- በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋፅኦ ያላቸው ኘሮጀክቶች በቅድሚያ እየተለዩና የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውም በቅድሚያ እንዲታወቁ በማድረግ፣ እቅድ በማዘጋጀትና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ተሣታፊ በማድረግ የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚከናወንበት ሥርዓት እንዲዘረጋ መደረግ፤ የግምገማ ውጤቱም ሪፖርት ተዘጋጅቶለት ለውሣኔ ሰጪ አካላት ሊቀርብና በመረጃነትም ሊጠበቅ ይገባል፡፡

57. <u>ለዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሚከናወነው የመኖ፣ ውሃ እና ግጦሽ መሬት አቅርቦት፣ የጤና አጠባበቅ፣ የግንዛቤ መዳበርና ሥልጠናን በተመለከተ የተካሄደ ክዋኔ ኦዲት</u>

- በየአካባቢው ካለው ፍላጎት ጋር የተመጣጠነ የዳልጋ ከብት መኖ አቅርቦት በእጅጉ ያነሰና የሰብል ተረፈ ምርት የማቀነባበርና ለገበያ የማቅረብ ሥርዓትም ያልተዘረጋ መሆኑ፤

- በሀገር ውስጥ በስጋ ምርታቸው የተሻለ ምርት በሚሰጡት ላይ ጥናት ተደርጎ በደረጃ የቦረና፣ የፎገራ እና የከረዩ የመሳሰሉት ጥሩ ምርት መስጠት እንደሚችሉ ቢታወቅም፤ በሥጋ ምርት ዙሪያ የዝርያ ማሻሻያ ተግባር ግን አለመጀመሩ::

- በመሆኑም በእንስሳት ሀብት ልማቱ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት እንዲያስችል በእንስሳት ሀብት ልማቱ ላይ የሚመክር ብሔራዊ የጋራ የምክክር መድረክ ቢቋቋም በዘርፉ ላይ ያሉ መሠረታዊ ችግሮች እና አንገብጋቢ ጉዳዮችን በቅደም ተከተሉ የሚለይበት፣ የመፍትሔ እርምጃ በጋራ እና በተናጠል የሚወሰድበት ሥልት የመንደፍና ተፈፃሚ የማድረግ እርምጃ እንዲወስድ በማሳሰብ የማሻሻያ ሀሳቡን ሰጥቷል፡፡

58. <u>የመንግሥት ተሽከርካሪዎች አጠባበቅ፤ አጠቃቀምና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት</u>

- በሀገሪቱ ለመንግስት ተሽከርካሪ ግዥ፣ ጥገና፣ የነዳጅና ቅባት፣ ወዘተ… የሚወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ30 ዓመታት በፊት የተዘጋጀ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የሚተዳደሩበት መመሪያ እንዲሻሻል አለመደረጉ ወይም ወቅታዊ የሆነ መመሪያ አለመኖሩ፤ የመንግሥት ተሽከርካሪዎችን አስተዳደር በቁጠባ እና በብቃት እንዳይከናወን እንዲሁም ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ እንዳይቻል ማድረጉ፤

- የመንግስት መ/ቤቶች በኃላፊነታቸው ሥር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በምን መልኩ እንደተረከቧቸው፣ የተጓዙበት ኪሎ ሜትር ብዛት፣ የተጠቀሙበትን ነዳጅ፣ ቅባት እና ሌሎች ተዛማጅ ቁሳቁሶችን መጠን፣ የተደረገላቸውን ጥገና

እና ተያያዥ ወጪዎችን የሚመለከቱ ዝርዝርና ተገቢ መረጃዎችን የማይይዙ መሆኑ፤

- የተሽከርካሪዎች መጥፋት፣ ከመ/ቤቶቹ እውቅና ውጭ መሸጥ፣ በአሽከርካሪዎች ጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት የተሽከርካሪዎች መገልበጥ፣ ያልተወገዱ ተሽከርካሪ አካሎች በቦታቸው አለመገኘት፣ የተሽከርካሪ ሞተሮች መጥፋት እና የተሽከርካሪ ሞተሮች ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በወቅቱ ሳይወገዱ ለፀሐይ፣ ለዝናብና ለአቧራ ተጋልጠው መገኘት፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች አጠባበቅ ላይ ድክመት መታየቱ በጣም ከፍተኛ ዋጋ እና ግምት ያለው ሀብት ለብክንት እንዲዳረግ መንገድ የሚከፍት ከመሆኑም በላይ የመንግስት ተሽከርካሪዎች በኃላፊነት በተረከባቸው አካል በቂ ጥበቃ እየተደረገላቸው አለመሆኑ፤

- አብዛኛዎቹ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አዲስ ተገዝተው ሲገቡ አብሯቸው የሚገባ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ (fire extinguisher) ያላቸው ቢሆንም፤ አጠቃቀማቸው የማይታወቅና ሲያልቁና ሲበላሹ እንዲሁም የአገልግሎት ጊዜያቸው ሲያበቃ በየወቅቱ ክትትል የማይደረግላቸውና ለሚጠቀሙበት ሰራተኞች ስለአጠቃቀሙ ስልጠና የማይሰጥ መሆኑ፤

- የመንግስት ተሽከርካሪዎች በብቃትና በቁጠባ ለመጠቀም እና ለመጠበቅ የሚያስችል የተሟላ የሰው ኃይል በመመደብ ተሽከርካሪዎችን በአግባቡ ለማስተዳደር፤ ደንብና መመሪያዎችን ወቅታዊና ተግባራዊ በማድረግና የመንግስት ተሽከርካሪዎችን መረጃ በተገቢው መንገድ በማጠናቀር ውጤታማ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

59. <u>ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተመደበው ሀብት ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ የተካሄደ ክዋኔ ኦዲት</u>

- የሀገር አቀፉን የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ ፈቃድ ሳያገኝ በአጠቃላይ ብር 201,449,630.00 እና የአሜሪካ ዶላር 1,623,466 በተለያዩ መ/ቤቶች እና በክልል ጽ/ቤቶች ከተፈቀደለት ተግባር ውጭ ወደ ሌላ እንዲተላለፍ መደረጉ፤

- ከግሎባል ፈንድ ተገኝቶ ለአስፈጻሚ አካላት ተሰጥቶ ሳይወራረድ የቆየ (የዕርዳታ ውል ስምምነት ጊዜው የተጠናቀቀ) በድምሩ ብር 752,420,349.00 ሲኖር ከዚህ ውስጥ በድምሩ ብር 624,324,142 ማለትም ካልተወራረደው ገንዘብ 83% የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በሥሩ ያሉ መ/ቤቶችን መያዙ፤

- በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዙሪያ በተከናወኑ የፋይናንሻልም ሆነ የፊዚካል ሪፖርቶች ወጥና ተከታታይ ያለመሆን፣ ድግግሞሽ ያለባቸው እና በየሦስት ወሩ ወቅቱን ጠብቀው እንደማይላኩ፤

- የተለያዩ የመንግስት ሴክተሮችና አስፈጻሚ አካላት ለፀረ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተግባራት የተላከላቸውን ገንዘብ በወቅቱ እንደማይጠቀሙ፣ ተገቢውን ክትትል የማያደርጉ፤ የማወራረጃ ጊዜ ገደብ ሲቃረብ ብቻ በመሯሯጥ ገንዘብ ለመጠቀም ጥረት ስለሚያደርጉ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ መሆኑ፤

- በአገር አቀፍ ደረጃ በፌዴራል ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት አማካኝነት ወጥ የሆነ ገቢ ማስገኛ፣ የምግብ ድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎት መስጫ ደረጃ ተዘጋጅቶ አለመሰራጨቱ፤

- በመሆኑም ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተገኘውና የተመደበው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ጽ/ቤቱ ሕግና ደንብን ተከትሎ መፈጸምና የሚመለከታቸው አካላትም ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

60. <u>በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የቅርስ ጥናትና ጥበቃን በተመለከተ የተካሄደ ክዋኔ ኦዲት</u>

- ባለሥልጣኑ የማይዳሰሱ (intangible) ቅርሶች መመዝገቢያ መመሪያ ያዘጋጀ ቢሆንም ለተንቀሳቃሽ እና ለቋሚ ቅርሶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የቅርስ ምዝገባ ለማከናወን የሚያስችል ወጥ የሆነ መመሪያ ባለመውጣቱ የቅርስ አመዘጋገብ ሥራው ጥራቱን የጠበቀ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ለቀጣይ የቅርስ አጠባበቅ፣ ጥገና እና እንክብካቤ ሥራ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ፤

- ባለሥልጣኑ በተወሰኑ ክልሎች በማይዳሰሱ ቅርሶች ላይ ምዝገባ ያከናወነ ቢሆንም፣ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል የማይዳሰሱ (intangable) ቅርሶች ያልተመዘገቡ በመሆኑ በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች የማይዳሰሱ ባሕላዊ ቅርሶች ትኩረት አለመስጠቱ፣

- ከጥናትና ምርምር ባለሙያዎች ከሚገኘው አሥር በመቶ ገቢ ውስጥ ሃምሣ በመቶ ለቅርሱ ቦታ ማልሚያ እንዲውል መመሪያ ቢኖርም፣ ገቢው ለክልሎቹ የማይላክ እና ጠቅላላ የተሰበሰበው አስር በመቶ ባለስልጣኑ የሚያስቀር በመሆኑ፣ ከቅርስ ጥናትና ምርምር የሚገኝ ገቢ ለቅርስ ጥበቃ፣ ጥገናና ልማት ካልዋለ በጥበቃና ጥገና እጦት ትልልቅ ቅርሶችን ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችል መሆኑ፣

- ባለስልጣኑ እና ክልሎች በቅርስ አመዘጋገብ፣ አጠባበቅ እና ጥገና ላይ ያላቸው የሥራ ድርሻ በግልፅ ባለመቀመጡ፣ የተቀናጀ ሥራ ለማከናወን እንዳይቻል የሚያደርግና በቅርሶች ዙሪያ ሊሠሩ የሚገቡ ሥራዎች በወቅቱ እንዳይሠሩ እና ባለቤት እንዲያጡ በማድረግ ለብልሽት እና ለጥፋት የሚያጋልጥ መሆኑ፣

- በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርስ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ የመረጃ ልውውጥ በማድረግና በቅንጅት በመስራት ቅርሶች የሚመዘገቡበት፣ የሚጠበቁበትና እንክብካቤ የሚያገኙበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

61. <u>በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የዕቃ ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የተካሄደ ክዋኔ ኦዲት</u>

- በኮርፖሬሽኑ በናሙና በታዩት ስምንት ግዥ ፈፃሚዎች የሚፈጸሙ ግዥዎች በሙሉ በእቅድ (procurement plan) ላይ ያልተመሰረቱና ግዢዎች በየጊዜው በተነጣጠለ ሁኔታ በዋጋ መሰብሰቢያ (ፕሮፎርማ) በ2002 በድምሩ ብር 25,067,961.72 የተገዛ መሆኑ፣

- በናሙና ተመርጠው ከታዩ 14 ግዥዎች ውስጥ በሁሉም ግዥው ከመፈፀሙ በፊት የዕቃዎች ጥራት ለማረጋገጥ ለቴስት ዊትነስ ወደተለያዩ አገራት የሚሄዱ

ሰራተኞች ዕቃዎቹ ተገዝተው ንብረት ክፍል ገቢ በሚሆኑበት ወቅት በታየው ስታንዳርድ መሠረት ገቢ መሆናቸውን የማያረጋግጡ መሆኑ፤

- በናሙና በታዩት አስራ ሁለት ዕቃ ግምጃ ቤቶች ውስጥ በጎፋ፣ በድሬዳዋ፣ ሻሸመኔ፣ ሀዋሳ በሚገኙ ዕቃ ግምጃ ቤቶች በመጋዘን ውስጥ ሊቀመጡ የማይችሉ ንብረቶች ለፀሀይ፣ ለዝናብና ለአፈር ተጋልጠው እና በግቢው ውስጥ ተዝረክርከው ቢጠፉ እንኳን በማይታወቅበት ሁኔታ ሳር በቅሎባቸውና አቧራ ለብሰው ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

- የኮርፖሬሽኑ ቋሚ ንብረቶች አስፈላጊው የመድህን ዋስትና ሽፋን በተሟላ ሁኔታ የተገባላቸው አለመሆኑ እና የመድህን ዋስትና የተገባላቸውም የንብረቶችን ዋጋ ያላገናዘበ ወይንም በጥናት ያልተደገፈ መሆኑን፤

- ለኃይል ማመንጫነት ከሚውሉ ጄኔሬተሮች በናሙና ተመርጠው ከታዩት 3 የኃይል ማመንጫ ጄኔሬተሮች ውስጥ ቃሊቲ የሚገኘው የዲዝል ኃይል ማመንጫ 14.0 ሜጋ ዋት ማመንጨት ሲገባው የሚያመነጨው 3.5፣ አዋሽ 7 ኪሎ 35 ሜጋ ዋት ማመንጨት ሲገባው የሚያመነጨው 21 ሜጋ ዋት መሆኑ እና ድሬዳዋ 38 ሜጋ ዋት ማመንጨት ሲገባው ምንም እንደማያመነጭ፤ እንዲሁም የነበረውን የኃይል እጥረት እንዲያቃልሉ ኮርፖሬሽኑ 60 ሜጋ ዋት የሚያመነጩ ጄኔሬተሮችን ተከራይቶ ለኪራይ 10,368,000 USD ወጪ ማድረጉ፣ ነገር ግን የኮርፖሬሽኑ ንብረት የሆኑት ጄኔሬተሮች በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት ቢሰጡ 62.5 ሜጋ ዋት ማመንጨት ይችሉ እንደነበረና ለኪራይ የወጣውን ወጪ ሊያስቀር ይችል እንደነበር ተገምግሟል፡፡

- በመሆኑም ኮረፖሬሽኑ የታዩትን ችግሮች በመፍታት የግዥ ስርዓቱንና ንብረት አስተዳደሩን ዘመናዊ በማድረግ ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ ስራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

62. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተር በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በጊዜ ገደብ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ይህንኑ ድንጋጌ መነሻ በማድረግ መ/ቤታችንም አዲስ የክትትል ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት እንደተጠናቀቀ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ለተገኙባቸው 80 እና 14 የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች የማስተካከያ መርሃ-ግብር ነድፈው እንዲያሳውቁን ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም እስከአሁን መርሀ-ግብሩን የላኩት 34 መ/ቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያለመውሰድ የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ የእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ም/ቤቱም በዚህ ረገድ የሚያደርገውን ክትትልና ቁጥጥር ማጠናከር ይኖርበታል፡፡

የሪፎርም ሥራን በተመለከተ

63. በመ/ቤታችን የተካሄደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ተጠናቅቆ፣ የኦዲቱ ከየካቲት 2002 ጀምሮ የሌሎች ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ደግሞ ከግንቦት 2002 ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ከመዋሉም በላይ በመጀመሪያው የአንድ ዓመት የትግበራ ጊዜ የተገኘው ውጤት እጅግ አጥጋቢና ተስፋ ሰጪ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይልቁንም በጥናቱ እንደሚሚሉ ታሳቢ የተደረጉት ገብአቶች ቢሟሉ ኖሮ ውጤቱ አሁን ከተገኘው በእጅጉ ሊልቅ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

64. የተገኘውን ውጤት ይበልጥ ለማስፋት፣ ተቋማዊና ዘላቂ ለማድረግ ጥናቱን ተከትሎ አዲስ ተቋማዊ የአምስት ዓመት የስትራቴጂ ዕቅድ፣ የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂና የመረጃ ቴክኖሎጂ ስትራቴጂዎች ተቀርጸው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ናቸው፡፡ የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂው ትኩረት የባለሙያዎቹን ክህሎትና

እውቀት በመገንባት ከፍተኛ የሙያ ሥነ-ምግባርን የተላበሰና እሴት ያለው አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ፕሮፌሽናል ሠራተኛና ተቋም መፍጠር ነው፡፡ በሌላ በኩል የመረጃ ቴክኖሎጂው ስትራቴጂ ትኩረት የመረጃ አሰባሰብ፣ ትንተናና ልውውጥ እንደዚሁም የክምችት ሥርዓቱን ፈጣን፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የኦዲት ጥራት፣ ሽፋንና ወቅታዊነት ከፍ በማድረግ የኦዲት ወጪ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ ማስቻል ነው፡፡

65. የሰው ሀብት ልማትና የመረጃ ቴክኖሎጂ ስትራቴጂዎቹ በአሁኑ ወቅት በመተግበር ላይ ሲሆኑ ትግበራውም የሚካሄደው ከዕርዳታ ሰጪዎች በተገኙ ድጋፍ በመሆኑ የዕርዳታ ሰጪዎች ድጋፍ ሲቋረጥ አሁን የተገኘው ውጤት እንዳይስተጓጎል የዘለቄታው ጉዳይ በምክር ቤቱ ዘንድ ትኩረት አግኝቶ ተገቢው ሊመቻች ይገባል፡፡

66. በሌላ በኩል የሪፎርሙ አካል የሆነው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቱን ተከትሎ ለም/ቤቱ ቀርቦ የነበረው የመ/ቤታችን መዋቅርና የደመወዝ ስኬል ከረጅም ጊዜ በኋላ በቅርቡ ጸድቆ በመመለሱ የሠራተኛ ቋሚ ምደባ የተደረገ ቢሆንም የተፈቀደው ደመወዝ ከመ/ቤታችን ልዩ ባህርይና ባለሙያዎቹ በገበያ ላይ ካላቸው ከፍተኛ ተፈላጊነት አንፃር ችግሩን የሚያቃልል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ልዩ ትኩረት አግኝቶ እንደገና ሊታይ ይገባል፡፡

67. በአጠቃላይ ሲታይ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቱ ያስገኘው ውጤት እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በሂደት ያሉ ግብአቶች ከተሟሉ አሁን ከተገኘውም ውጤት የበለጠ ሊገኝ እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የም/ቤቱ ድጋፍና ትብብር ይበልጥ ሊጠናከር ይገባል፡፡

<u>የግንዛቤ ማዳበሪያና የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን በተመለከተ</u>

68. የኦዲት አሠራርና ጠቀሜታ እንደዚሁም፣ ተጠያቂነትን ከማስፈን አንፃር የሚኖረውን ፋይዳ በተመለከተ የተለያዩ የግንዛቤ ማዳበሪያ መድረኮች ተዘጋጅተው ለም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ አባላትና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ኃላፊዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ይህንን ሥልጠና ተከትሎ ወደ ም/ቤቱ በሚቀርቡ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ የሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር ከመጠናከሩም በላይ

የመንግሥት መ/ቤቶች ኃላፊዎችም ለኦዲት ሥራ የሚያደርጉት ድጋፍ በአብዛኛው መሻሻል አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን እንደዚሁም መልካም አስተዳደርን ከማጠናከርና ከማስፈን አንጻር ኦዲት ይበልጥ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የተጀመሩት የክትትልና የድጋፍ ሥራዎች በሁሉም ዘንድ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

69. በኦዲት ተደራጊዎችና በመ/ቤታችን መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በሥርዓት ለመምራትና አንዱ ከሌላው የሚፈልገውን ጉዳይ አስቀድሞ በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ እንዲሆን ለማድረግ “የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ፕሮቶኮል” የሚል ሠነድ ተዘጋጅቶ በውይይት ከዳበረ በኋላ ለሁሉም ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች እንዲሠራጭ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ኦዲት ተደራጊዎች ኦዲተሮቻችን የሚከተሉትን የሙያ ሥነ ምግባር እንዲያውቁና ክትትልም ለማድረግ እንዲያስችላቸው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲተሮች የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ ለሁሉም ባለበጀት መ/ቤቶች ተሠራጭቷል፡፡

70. ከሚዲያ ጋር ያለው ግንኙነትንም በሥርዓት ለመምራት እንዲያስችል የሚዲያ ፖሊሲ የተዘጋጀ ሲሆን በሠነዱ ላይ የመንግሥትና የግሉ ሚዲያ ተቋማት እንዲወያዩበት ተደርጎ የሚዲያ ፖሊሲው በሥራ ላይ ውሏል፡፡

<u>ሴክተር ዘለል የሆኑ ሥራዎች በተመለከተ</u>

71. በሥርዓተ ጾታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ፣

- እንደአዲስ ከተቋቋሙት ኮሚቴዎች መካከል የሴቶች ጉዳይ በአጭር ጊዜ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለሁለተኛ ጊዜ በመ/ቤታችን የማርች 8 ቀን እንዲከበርና በተጋባዥ የሴቶች ጉዳይ ባለሙያ በቀረበ የሥርዓተ ፆታ ትምህርት ሠራተኛው ግንዛቤ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡
- የዓመቱ የአለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል “የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ሁሉ አቀፍ ተደራሽነትና ሰብአዊ መብት (Universal Access & Human rights)” መልእክት በማስተላለፍ ሠራተኛው የዓመቱ የዓለም የኤድስ ቀን

መሪ ቃልና የቀይ ሪቫን መልዕክት በደረት ላይ በማድረግ እርስ በእርስ እንዲወያዩ ተደርጓል፣

- መታቀብ፣ ካልሆነም አንድ ለአንድ መወሰን እንደሚቻል በመመርመር እራስን በማወቅ ጤንነታችንን ለመጠበቅ የሚያስችል ጽሑፍና ሌሎች ብዛት ያላቸው ብሮሸሮችና በራሪ ወረቀቶች በላይብረሪ እንዲቀመጥና በመ/ቤቱ ህንፃዎች ላይ እንዲለጠፉ ተደርገዋል፣
- በሶሻልና ኢንቫሮሜንት ኮሚቴ አስተባባሪነት የመ/ቤቱ ሠራተኛ በሙሉ የተሳተፈበት የ2002 የችግኝ ተከላ ፕሮግራም በኦሮሚያ ክልል ገላን ከተማ ተከናውኗል፡፡

ለኦዲተሮችና የሂሳብ አዋቂዎች የሙያ ማረጋገጫ መስጠትና መከታተልን በተመለከተ

72. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5/16 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከጥር 2002 እስከ ታህሣሥ 2003 ባለው ጊዜ ለ7 የግል ኦዲተሮችና 80 የግል ሂሣብ አዋቂዎች አዲስ የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጥቷል። ቀደም ሲል ፈቃድ በተሰጣቸውም ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል፡፡

73. ሆኖም አንዳንድ ግለሰቦች ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወይም ከተፈቀደላቸው ውጪ የኦዲትና የሂሣብ አገልግሎት ሲሰጡ በመገኘታቸው የአገልግሎት ተጠቃሚ ህብረተሰብን ከህገ ወጦች ለመከላከል ሲባል 47 የተፈቀደላቸው ኦዲተሮችና 323 የሂሣብ አዋቂዎች የስም ዝርዝራቸውን በመ/ቤቱ ዌብ ሣይትና፣ በጋዜጣ እንዲወጣ እንደዚሁም በደብዳቤ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች የተገለጸ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሚንቀሳቀሱ ሲያጋጥሙ ለእርምጃ አወሳሰድ እንዲያመች ለመ/ቤታችን ጥቆማ የሚቀርብበትን ሥርዓት ኅብረተሰቡ እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡

74. በሌላ በኩል የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በጠየቁት መሠረት በየደረጃው ለሚገኙ 58 ለሚሆኑ የውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ደረጃ ማረጋገጫ ተሰጥቷል።

75. በም/ቤቱ ፀድቆ የወጣው በግል የሚሠሩ ኦዲተሮችና የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ደንብ እና የግል ኦዲተሮችና የሂሣብ

አዋቂዎች ሊከተሉት የሚገባ የሙያ ሥነ-ምግባር በተመለከተ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የአንድ ቀን አውደ ጥናት ተዘጋጅቶ ውይይት ከተካሄደ በኋላ ሠነዱ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

76. የግል ኦዲተሮችና የሂሣብ አዋቂዎች ፈቃድ አሰጣጥ በመ/ቤታችን የተካሄደውን የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትን ተከትሎ ከፌዴራል ዋና ኦዲተር እንዲወጣ ለማስቻልና ሌሎች የሀገሪቱን የፋይናንሻል ሪፖርቲንግ ጉዳዮችንም ሥርዓት ለማስያዝ የረቂት የፋይናንሻል ሪፖርቲንግ ህግ ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ

77. መ/ቤቱ በፀደቀው አዲስ መዋቅር መሠረት 381 የኦዲት ባለሙያዎች እና 192 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 573 ሠራተኞች የሚኖሩት ሲሆን በአሁኑ ወቅት ሥራ ላይ ያሉት 233 የኦዲት ባለሙያዎችና 141 የድጋፍ ሰጪ በድምሩ 374 ሠራተኞች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ከጥር 2002 እስከ ታህሣሥ 2003 ባለው ጊዜ 32 የኦዲት ባለሙያዎችና 14 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 46 ሠራተኞች በተለያዩ ምክንያት ሥራ ለቀዋል፡፡

የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ

78. በ2002 በጀት ዓመት ለመ/ቤታችን የተፈቀደው በጀት ብር 12,215,500 ሲሆን ሥራ ላይ የዋለው ብር 12,109,077 ወይም ከበጀቱ 99% ሆኗል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች

79. መ/ቤታችን በሕገ መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም በአንዳንድ ችግሮች ምክንያት ያሰበውን ያህል መራመድ አልቻለም፡፡ ካጋጠሙት ችግሮችም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ኦዲቱን በሚፈለገው መጠንና ጥረት ለማከናወን የሚያስችል በቂ ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ መቅጠርና መያዝ አለመቻል፣

- ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ሂሣባቸውን በወቅቱ ዘግተው ለኦዲቱ አለማቅረብ፣

- ኦዲት ተደራጊዎች በሚሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረት በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ፣

- ለኦዲት ሥራው አንደኛ ዋንኛ ግብዓት የሆነው የኮምፒዩተርና ተዛማጅ ዕቃዎች ግዥ ረጅም ጊዜ መውሰድ፡፡

የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ

80. መ/ቤታች አዲሱን አሠራር መተግበር ከጀመረበት የካቲት 2002 ጀምሮ የሂሣብ መዘጋትን ሳይጠብቅ የበጀት ዓመቱን ሂሣብ ኦዲት በጥር ወር በመጀመር በተከታይ የበጀት ዓመት ታህሣሥ ላይ ለማጠናቀቅ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ የክዋኔ ኦዲትን ደግሞ በዓመቱ 36 ለመሥራት በጥራት ተደራሽ ግብ የተጣለ መሆኑም ይታወቃል፡፡ ይሁንና የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቱን ተከትሎ ለም/ቤቱ ቀርቦ የነበረው መዋቅር ዘግይቶ በመፅደቁና የታሰበው የሰው ኃይል ባለመሟላቱ የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲቱን ሽፋን 92.36%፣ የክዋኔ ኦዲትን ደግሞ በቁጥር 22 እና የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ተከታታይ ኦዲትን በቁጥር 258 ለማከናወን ታቅዷል፡፡

81. በዚሁ መሠረት ከጥር እስከ ሚያዝያ 2003 ባሉት አራት ወራት ጊዜ 80 የፋይናንስና ሕጋዊነት፣ 17 የክዋኔ እና 72 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲቶች ተጀምረው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በላይ በአጠቃላይ የኦዲቱ ሥራ በታቀደው መሠረት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

82. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በውጭ ሀገር መንግሥታት ድጋፍ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የዕርዳታ ሂሳቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል። ሆኖም ራሱ ከሚሰራው

በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል:: በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

83. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2002 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወኑ ኦዲቶች የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶች የሂሣብ መግለጫ ሁኔታ

84. በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 99 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ደግሞ 131 በድምሩ 230 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የአንድ መ/ቤት የሁለት እና ከዚያ በላይ ሂሳብ ኦዲት የተደረገ ከሆነ የቅርቡን በጀት ዓመት ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ኦዲቶች ተወክውኗል፡፡

85. በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified opinion) የቀረበበት 95፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት (Qualified opinion) የቀረበበት 129፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት (Disclaimer opinion) የቀረበበት 6 በድምሩ 230 ናቸው፡፡

86. በሌላም በኩል እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም. መጨረሻ ባለው መረጃ መሠረት ከሁለት ዓመታት በላይ ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 43 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይገኛሉ፡፡ የኦዲት አንዱ ጠቀሜታ ወቅታዊ የሆነ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ስለሆነ ከረጅም ጊዜ በኋላ ኦዲት ተደርጎ የሚቀርበው ሪፖርት እርምጃ ለመውሰድ አስቸጋሪ በመሆኑ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት

ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እነዚህ ድርጅቶች ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት እንዲያስደርጉ በቅርበት ሊከታተል ይገባል፡፡

የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን
የሥራ እንቅስቃሴና ያጋጠሙ ችግሮች

87. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 የተቋቋመ ሲሆን፣ ዓላማው፤ የመንግሥት ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት ማበርከት ነው።

የሥራ ክንውን

88. በ2002 በጀት ዓመት በነበረው 122 የሰው ኃይል 257 ኦዲቶችን ለማድረግ አቅዶ 222 ኦዲቶችን ወይም የዕቅዱ 86.38% ለመፈጸም ችሏል፡፡ በዚህ መሠረት ከዕቅዱ በ35 ኦዲቶች ወይም (13.62%) ዝቅ ያለ ሲሆን፣ ለዚህም ምክንያቱ እንደተጠበቀው ከኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች ረቂቅ የሂሣብ መግለጫዎች ለምርመራ ባለመቅረባቸውና ምርመራውም ተጠናቆና ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ነገር ግን ውይይቱ በበጀት ዓመቱ ባለመጠናቀቁ ወደሚቀጥለው በጀት ዓመት በመተላለፋቸው ነው፡፡ ከዚህም በላይ በበጀት ዕቅዱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሰራተኞች ድንገት ሳያሳውቁ በፈቃዳቸው ሥራ በመልቀቃቸው የሰው ኃይሉ በመሳሳቱ ነው፡፡ ሆኖም ከ2001 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ32 ሪፖርት ወይም በ17% ብልጫ አሳይቷል፡፡

የፋይናንስ እንቅስቃሴ

89. ኮርፖሬሽኑ በ2002 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 7.8 ሚሊዮን ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 8.5 ሚሊዮን ገቢ አግኝቷል፡፡ በሌላም በኩል ብር 6.8 ሚሊዮን ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 6.2 ሚሊዮን ወጪ ያደረገ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ የብር 2.2 ሚሊዮን ትርፍ ሊያገኝ ችሏል።

ኮርፖሬሽኑ ባካሄዳቸው ኦዲቶች የታዩ አጠቃላይ ችግሮች

90. ኮርፖሬሽኑ ባካሄዳቸው ኦዲቶች የታዩ አጠቃላይ ችግሮች በርካታ ሲሆኑ በተለየ ጥራዝ በቀረበው ዘገባ በዝርዝር የተጠቀሱ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ፤

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ ዝርዝር መዝገብ የሌላቸው፣ ያላቸውም ቢኖሩ ደግሞ ብዙዎቹ መዝገባቸው ያልተሟላ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን በአንድ ላይ መዝግበው የተገኙ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን የሚገኙ ዕቃዎችን ቆጠራ የማያደርጉ መሆናቸው፣ አንዳንዶቹ በከፊል ቆጠራ የሚያደርጉ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ቆጠራ ቢያደርጉም ከሂሣብ መዝገብ ጋር የማይገናዘብ መሆኑ፣
- አብዛኞቹ ድርጅቶች በርካታ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ የተገኘባቸው ሲሆን ሂሳቡን ለመሰብሰብ ተገቢውን ጥረት ያላደረጉ ከመሆኑም በላይ አጠራጣሪ ለሆኑት ተሰብሳቢ ሂሣቦች በቂ መጠባበቂያ ያልያዙ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበሰብ ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ ከመሆኑም በላይ አልፎ አልፎ ከተሰበሰበው ገንዘብ ላይ ክፍያ የሚፈጽሙ መሆኑ፣
- በርከት ያሉ ድርጅቶች ለመንግሥት መክፈል የሚገባቸውን ከደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ መዋጮ እንዲሁም የንግድ ትርፍ በወቅቱ የማይከፍሉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ አለመዝጋታቸውና እንዲዘጉም የሚደረገው ግፊት የሚፈለገውን ያህል አለመሆኑ፣

- አንዳንድ ድርጅቶች ተከፋይ ብለው ከያዙት ሂሣብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሣይከፈሉ የቆዩና ለማን መከፈል እንዳለባቸው የማይታወቁ ሂሣቦች መኖሩ፣

ናቸው፡፡

ማጠቃለያ

91. በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው የኦዲት ሽፋን ከ87% በላይ ደርሷል፡፡ ውዝፍ የኦዲት ሥራ ባለመኖሩ ወቅታዊ የኦዲት

መረጃን ማመንጨት ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት የሀገራችንን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የተሻለ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመለክት ቢሆንም በኦዲቱ ሂደት የተገኙት ዋና ዋና ግድፈቶች በአፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ዝርዝር ሪፖርቱ በ19 ጥራዝ ተዘጋጅቶ የቀረበ በመሆኑ ም/ቤቱ በጥልቀት መርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

92. በተለይ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ እርምጃ ሳይወሰድባቸው ከዓመት ወደ ዓመት የሚተላለፉ የሠነድ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተመሳሳይ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች ልዩ ትኩረት አግኝተው መርሀ-ግብር ወጥቶላቸው እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

93. በዚህ ረገድ በተለይ ኦዲት ተደራጊዎች በጊዜ ገደብ የታጠረ የማስተካከያ መርሀ-ግብር መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ የም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም የክትትልና ቁጥጥር ፕግሮራም በመንደፍና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በመታገዝ የግድፈቶቹን መንስኤዎች በማጣራት ከሥረ መሠረቱ ለማስወገድ ሊሠሩ ይገባል፡፡

94. በመጨረሻም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የቀረፃቸውን የአሠራር ማሻሻያዎችና ስትራቴጂዎችን በሚገባ በመተግበር ይበልጥ እንዲጠናከርና የምክር ቤቱን የክትትልና የቁጥጥር ተግባር በተሻለ ደረጃ እንዲያግዝ ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግለት እየጠየቅሁ በጥሞና ስላዳመጣችሁን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡